# ማን ያውራ የነበረ ቀ. 4

በሐምሌ 1982 ዓ.ም. ፈለገ ዴሞክራሲ ወይስ ከአንድ ፈላጭ ቆራጭ አገዛዝ ወደ ሌላ? በሚል ርዕስና በነሐሴ 1982 ዓ.ም. ቅይጥ ኤኮኖሚ፤ቅይጥ ሂደት፤ ቅይጥ ጎራ በሚል ኢሕአፓ ሁለት (ባለ 63 ባለ 33 ገፆች) ፅሁፎች አውጥቶ ከደርግም ከወያኔም በፖለቲካወና በኤኮኖሚው ጥያቄ ላይ ያለውን ልዩነት ግልፅ አድርጎ ነበር፡፡የፖሊተካ አቅዋምን ማድበስበስ ሳይሆን ግልፅ አድርጎ ማስቀመጥ ወሳኝ ነው፡፡ ሕዝብ ማን ማን መሆኑን ማወቅ ያለበት ሲሆን የሕዝብን መፈክር አወናባጅ ገዢ ኃይል ለራሱ ግልጋሎት እንዳያውለውም ያግዳል፡፡ ደርጉ ለምሳሌ የመሬት አራሹንና ሌሎች መፈክሮቸንም በሌጣው ወስዶ ሊጠቀምበትምና ተቃራኒውን ሊያደርግ መሞከሩን አይተናል፡፡ ወያኔም በዴሞክራሲና በመድብለ ፓርቲ ስም በተለጣፊ የታጀበ አምባገነናዊ አገዛዙ ማስፈኑን እያየ ነው፡፡

ለዚህም ነው ደጋግመን ኢሕአፓና የዴሞክራሲ መብት ጥያቄ በሚለው ላይ አቋማችንን በግልፅ ማስቀመጥ ያለብን፡፡ ኢሕአፓ ከተመሰረተ ጊዜ ጀምሮ ለሕዝብ ያልተገደበ ዴሞክራሲያዊ መብት ታግሏል፡፡ አንዳንድ ከታሪክ የተጣሉ ግን ካልተቸን ባይ ክፍሎች፥ ለምሳሌ ደርግም፤ወያኔም ኢሕአፓም ፕሮግራማቸው አንድና ያው ነበር ሲሉ ተደምጠዋል፡፡ በመራራ ትግልና ቅራኔ ደም የፈሰሰውም እንዲያው በግለሰቦች ሹክቻ እንጂ በመሰረታዊ የአቋም ልዩነት አልነበረም እስከማለትም ደርሰዋል፡፡ ይህ ከሀቅ የተጣላ ልፈፋ ኢሕአፓ ለዴሞክራሲ ያደረገውን መራራ ትግል፤ ከቶም አይረዳም ፤ቦታ አይሰጥም፡፡ ኢሕአፓ ከደርግ ጋር ገና ከጥዋቱ ሲታገል ሰፊ ሕዝባዊ መሠረት ያለው መንግሥት ይቋቋም ያለ ሲሆን መመስረት የሚገባው ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግሥትም ሁሉንም የፖለቲካ ኃይሎችና የሕዝብ ወኪሎች ያሳተፈ መሆን አለበት ብሎም ግልፅ አድርጎ ነበር፡፡ ዴሞክራሲ አለገደብ ለሰፊው ሕዝብ ብሎ በ1967 ዓ.ም. ፕሮግራሙ አስፍሮ የታገለው የደርግን የአንድ ኃይል ፈላጭ ቆራጭነት በመቃወምና የሕዝብም መብት በማንም- ባልተመረጠ ኃይል ቀርቶ በተመረጠም ቢሆን-- ሊገደብ ከቶም አይችልም በሚል ነበር፡፡ ይህ መሠረታዊ ልዩነት--ማለትም ሥልጣንና መብት ለሕዝበ ወይስ ለጥቂቶች? በሚለው ላይ ያለው ልዩነት-- የሚታረቅ ቅራኔ ሰላልነበረና፥ ወታደራዊው መንግሥትም የሰላም ትግል ተቃራኒ ስለነበረ ጎራ ለይቶ መዋጋቱ የግድ ነበር፡፡ በዚህ ወቅት ከአረመኔው ደርግ ጎን ቆመው ሕዝብን ያፈኑና የመተሩ፤ ከኢሰፓአኮ እስከ ኢሰፓ የጭቆና ሥርዓቱን አጅበው የነበሩ፥ ዛሬ ተመልሰው በተገላቢጦሹ ኢሕአፓ ዴሞክራሲያዊ አልነበረም ብለው ሲተቹ፥ ተው የምንላቸውና ሊረሱ የፈለጉትን ታሪክ የምናስታውሳቸው ኢሕአፓ ከተመሠረተ ጀምሮ ለብዙሀኑ የኢትዮጵያ ሕዝብ መብት የታገለ ድርጅት በመሆኑ ነው፡፡

ታጋይ ድርጅቶች ነን የሚሉት ቀርቶ፥ ሥልጣን የያዙ ቡድኖችም ቢሆኑ፥ በዴሞክራሲ መማል መገዘት ልማዳቸው ሆኗል፡፡ አራት ኪሎ ቤተመንግሥት ሊገባ ወራት ሲቀረው እንኳን የመድብለ ፓርቲ ሥርዓትን አድሀሪ ብሎ ያወግዝ የነበረው ወያኔ ለምሳሌ ከምዕራቦቹ ለመጠጋት ቢያንስ በአፋዊ ደረጃ

አምባገናናዊና ስታሊናዊ ሥርዓት እመሰረታለሁ ያለውን ትቶ የኢሕአፓን አቋም ከእነ ቃሉ/መደብለ ፓርቲ የሚለውን/ ቀምቶ የብዙህን ፓርቲ ሥርዓት እነሆ ማለት ተገድዷል፡፡ በአፋዊ ደረጃ፡፡ በህቅ ግን ሥርዓቱ የአንድ ፈላጭ ቆራጭ ድርጅት ማለትም የህወሓት የበላይነት የሰፈነበት መሆኑን ያመያወቅ ኢትዮጵያዊ የለም፡፡ በአፋዊ ምንባብና በወረቀት ደረጃ፥ የመለስ አገዛዝ የሕዝብን መብት አከበርኩ ባይ መሆነን የማያውቅ ሕዝብ የለም፡፡ በህቅ ግን የአፈና ሥርዓት፤ዘረኛ ሥርዓት መመስረቱን እያየ ነው፡፡ ከገዢው ባሻገር ደግሞ ለሕዝብ እንታገላላን የሚሉ ድርጅቶች ሁሉ፥ እውነትም ለዴሞክራሲ ቆመዋል ማለት በደፈናው የሚቻል አይደለም፡፡ የሁሉንም የመደብ መሠረት፤ በገቢር ለማን ጥቅም እንደቆሙ፤ በገቢር ለብዙሀኑ ይሟገታሉ ወይስ የጥቀቶችን ጥቅም አስጠባቂ ናቸው? የሀገርን ሉዓላዊነት ያስቀድማሉ? ወይስ ዕትብታቸው ከባዕዳን ጋር ተሳስሯል? ወዘተ የሚሉትን አቢይ ጥያቄዎች ምላሽ መስጠት ያሻል፡፡ ሀጢያተኛ በአፉ ፃድቅ ነኝ ማለትን ያባዛልና በተጨባጭና በተግባር ሀቁን መገምገም የግድ ነው፡፡

ኢሕአፓ በሂደት ፕሮግራሙንና አቋሙን እያሻሻለና ከሕዝብ ፍላጎት ጋርም እያጣጣመ የሄደ ሲሆን፥ ወያኔ ለምሳሌ በ1981 ዓ.ም. ያወጣው የኢሕአዴግ ፕሮግራም ምንኛ ይህ ቡድን ከቅዠቱ መላቀቅ እንዳልቻለ የሚያረጋግጥ ነው፡፡ የግንቦት 1975 ዓ.ም. የህወሓት ሁለተኛ ድርጅታዊ ጉባዔ ያፀደቀው ፕሮግራምም ተመሳሳይ ነው፡፡ ይህንንና ሌሎችንም ከኢሕአፓው የ1983 ቀጣይ ፕሮግራሞች ጋር ማነፃፀር ያሻል፡፡ ኢሕአፓ፥ <u>ደሞክራሲ ስንል ዴሞክራሲ ሲሉ</u> በሚል ደግሞ ደጋግሞ የፃፈው እንዲያው ከሌሎች ልዩ ነኝ ለማለት ሳይሆን፥ መሠረታዊ ልዩነቱን ግልፅ አድርጎ ለማቅረብ ነው፡፡ ለሕዝብ ቆመናል እያሉ፥ የሕዝብን መብት በሰበብ አስባቡ የሚገድቡ ኃይሎች በመኖራቸው፥ ኢሕአፓ ዛሬም <u>ያልተገደበ ዴሞክራሲያዊ መብት ለብዙሀኑ</u> የሚለውን መፈክር ያስተጋባል፡፡ የሕዝብ ሰብዓዊ ዴሞክራሲያዊ መብቶች ሲልም፥ ብዙሀኑን የሚመለከቱና በፖለቲካውም፥ በኤከኖሚውም መስክ የሚገለፁ ናቸው፡፡ ይህም ማለት፡-

- በአፋኝ ህግ የማይገደብ ነፃ የፅሁፍና የፕሬስ ነፃነት፤
- የ ግግር ነፃነት፤
- የመደራጀት መብት፤
- በሀገር ውስጠም ወደ ውጪ ሀገር የመንቀሳቀስ መብት፤
- በፅሁፍም፤በሰላማዊ ሰልፍም፤ በሥራ ማቆም አድማም፥ በሰላማዊ መንገድ ተቃውሞን የማሰማት መበት፤
- ሙሉ የመምረጥና የመመረጥ መብት፤
- የብሄረሰብ፤ የፆታ፥ የሃይማኖት እኩልነት መብት፤
- የመሬት ባለቤትነት መብት፤
- ለጭፍን ብዝበዛ ያለመጋለጥ መብት፤
- የሴቶች የእኩልነት መብት፤
- የህፃናት መብት፤
- በህግ ፊት እኩል የመሆን መብት፤

- የጤና/ህክምናና የማግር መብት፣
- የጡረታ መብት
- ወዘተ

እነዚህን መብቶች ሁሉ÷ ኢሕአፓ የሚተረጉማቸውና በሥራ ያዋሉ የሚላቸው ብዙሀኑን÷ በቅድሚያም አርሶ አደሩን፣ ላባደሩንና ሰፊውን ሰረቶ አደር ሕዝብ በሚጠቅሙበት መንገድ ነው። ኢሕአፓ ከዓመታት በፊት ራዕዩን÷ ሶሻል ዴሞክራሲያዊ ብሎ ሲያቀርብ÷ ለሕዝብ የሚሆን ሰፊ ዴሞክራሲ የምታገል ነኝ ማለቱ እንደነበርም አይዘነጋም። በዚህ መንገድ እንጂ በሌላ መደራጀት አይቻልም፣ ከዚህ ቁጥር በላይ ድርጅት መኖር የለበትም፣ ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትስሩን አትተቹ አትሳለቁባቸው፣ መሪ ከተባልኩ ጣዖት ነኝና አምልኩኝ፣ የአርሶ አደሩ መብት መረገጡ አይቀሬ ነው፣ ላባደሩ መብዘበዙ የተፈጥሮ ህግ ነው፣ ነፃው ፕሬስ በህግ መገደብ አለበት፣ ሰላማዊ ተቃውሞ እኛ ስንፈቅድ ብቻ ነው፣ ተቃዋሚን ህገ ወጥ ማለት መብት አለን፣ የሴቶችን መብት መገደብ አለብን ወዘተ የሚሉ ሁሉ ዴሞክራሲያዊ ሳይሆኑ አምባገነናዊ ለመሆናቸው ጥርጥር ሊኖር አይገባም። የምርጥና የበላይነት ዝ ባሌ ያላቸው ክፍሎች፣ ከብረናልና ድህውን እንበዝብዝ የሚሉ ክፍሎች፣ ለራሳቸው ብልፅግና ሲሉ የፖለቲካ ሥልጣንን የሚሹ ወይም የሚጠቀሙ ኃይሎች ከኢሕአፓ ጋር የተቃረኑ ናቸው። በሀገራችን ኤኮኖሚያዊ ዕድገት መኖሩ አስፈላጊ ቢሆንም÷ መረን በለቀቀ ሰው ባለ ሥርዓት አማካኝነተና ሚለዮኖች ተጨፍልቀው ለሚመጣ ዕድገት÷ ኢሕአፓ ጠበቃ አይደለም። ነፃ ገበያ ቢልም ብሄራዊ ነጋዴዎችና አምራቾች ቅድሚያ እንዲሰጣቸውና እንክብካቤ እንዲደረግላቸው ይፈልጋል። ለተበዘበዘው ክፍል፣ ለተዘነጋው ሕዝብ ልዩ እንክበካቤን ይደግፋል። የሰርቶ አደሩ ሕዝብ የጤና፣የትምህርት፣ የጡረታ ዋስትና የትግሉ እምብርት ነው። ዴሞክረሲ በቅድሚያ ለብዙሀን የሚል ነውና÷ ሕዝባዊ ዴሞክራሲ፣ሶሻል ዴሞክራሲ ሲል÷ ለይስሙላ ሳይሆን÷ የትግሉ መሠረት በመሆኑ ነው።

ኢሕአፓ ቀደም ሲልም በውስጣዊ አደረጃጀቱ ÷ የዘቱና አሰራሩም ይህንኑ ያንፀባርቃል። ከልዩ ልዩ ብሔረሰቦች የመጡ ኢትዮጵያውያን አባል ሆነውና ሰምረው የሚታገሉበት ድርጅት ነው። ሴቶች በእኩልነትና በሁሉም የድርጅቱ እርከን ተገኝተው የታገሉበት/ የሚታገሉበት ድርጅት ነው። በጋራ አሰራር የሚያምን ድርጅት ነውና÷ በአመራርና በአባላት መሀልየአጉል ሹመት ገደል የለም። አሰራሩም የጋራ አመራር መርኅን የተከተለ ነውናአንድ ፈላጭ ቆራጭ መሪ ተብየ ወይም ሊቀመንበርና ዋና ፀሐፊ ሰይሞና ከፍተኛ ሥልጣን ሰጥቶ የአንድ ሰው ድርጅት አልሆነም። ይህንን የኢሕአፓን ዴሞክራሲያዊ ተመክሮ ከሌሎች ተመክሮዎች ጋር በማነፃፀር መገምገም ይቻላል። ኢሕአፓ በትጥቅ ትግል ተሰማርቶ ሳለም÷ ስንብት የሚጠይቅ የሠራዊት አባል የመሰናበት መብቱ የተጠበቀ ነበር። ደከመኝ በቃኝ ብለህል ብሎ ማንንም አባል እንደሌሎቹ ድርጅቶች አልረሸነም። ዛሬም የአባላቱና የአካላቱ የጋራ ጥረትና ትግል ነፀብራቅ እንጅ የአንድ በተክለ ሰውነት የተካነ መሪ መለያና

መሳሪያ አይደለም። ለዴሞክራሲ እንታገላለን ወይም ቆመናል የሚሉ ድርጅቶች በውስጣቸው- በድርጅታቸው ዴሞክራሲ መስፈን አለመስፈኑን ማረጋገጥ የግድና መቅደምም ያለበት ነው።

ኢሕአፓ ቀደም ሲል ከነበሩት ሥርዓቶችም ሆነ፥ ዛሬ ካለው ጋር በዴሞክራሲ ጥያቄ የማይናቅ ልዩነት አለው። ይህም በፕሮግራሙ ሰፍሯል። የብሄረሰብ እኩልነት ሲነሳ፥ እሬት እሬት ከሚላቸው ጋር ይለያል። የሰርቶ አደሩ ሕዝብ የመቃወም መብት ሲነሳ ሥርዓተ አልበኝነት መጣ ሊሉ ከሚቃጡ ጋርም አይስማማም። የሴቶች ሙሉ መብት ሲባል፥ ባህልንና ሃይማኖትን ተገን አድርገው መብትን ሊገደቡ ከሚወራጩት ጋር አይጠጣጣምም። አምራቹን ኃይል የላቡን ዋጋና ምርቱን ሊነጥቁ ከሚከጅሉት ጋር ጠብ አለው። ከባዕዳን ጋረ ዝምድና ቢልም፥ የሀገርን መሬት ለባዕድ ጦር ሰፈርነት አያቀርብም። ከባዕድ ገንዘብ ለማግኘት በሚል ፈሊጥ፥ የሀገርን ቁልፍ ወይም ስትራተጂያዊ ተቋሞችን አይቸበችብም። የኢሕአፓ ዴሞክራሲ፥ የማይናጋ ሀገር ወደድነትንና ለድርድር የማይቀርብን ሕዝባዊነት ያቀፈ ነው። ለዚህም ነው፥ ድርጅቱ ከወያኔ ጋር ብቻ ሳይሆን፥ ወያኔን እንቃወማለን እያሉ ዴሞክራሲን ሊገድቡ ከሚያቀነቅኑ ኃይሎች ጋር ልዩነት ያለው። የሰራተኛ ማህበራትን ማፈን ወይም ማገድ፤ የሕዝብ ድርጅቶችን ማፈን ወይም ማሳደድ፤ ተቃውሞን በጥይት ማስተናገድ፤ አፋኝ ህጎችን ማዠጎድጎድ፤ ሰፊውን ሕዝብ መለጎምና ከፖለቲካ ውሳኔ ማግለል፤ ነፀና ፍትኃዊ ምርጫን መፃረር፤ፍትህ ርትዕን ማራቅ ወዘተ የጨቋኝና ፀረ ዴሞክራሲ ሥርዓቶች ከልፈፉቸው ባሻገር፥ በተጨባጭ መለያዎቻቸው ናቸው። እስር ቤቶቻቸውም በፖለቲካ እስረኞች ይጨናነቃሉ።የሕዝብ ለቅሶና ዋይዋይታም በሀገሪቷ ሁሉ ይሰማል። ኢሕአፓ የዚህ ሁሉ ተፃራሪና ጠላት ነው።ለዚህም ነው ከ 15 ዓመት በፊት ባወጣው የዴሞክራሲያ ዕትሙ (ቅፅ 16 ቁጥር 2) የሚከተለውን ያሰፈረው፤

“ የአፄ ኃይለ ሥላሴ ሕገ መንግሥት ለሕዝብ ሰፋ ያለ ሕጋዊ መብት ደንግጎ ነበር። ፋሺስታዊው መንግሥት የደነገጋቸው መብቶች ደግሞ ዘየ ተረፍ ናቸው። ብዙ ታጋይ ድርጅቶችም ደርድረዋቸው የሚታዩ የሕዝብ መብቶች ያማልላሉ። ሆኖም ሙዳውን ሰጥቶ ካራውን እንደመሸሸግ ዓይነት ሰፊው ሕዝብ ባለመብት ነህ ተብሎ መበቱ የሚረጋገጥባቸውን፤ተጋፊ ሲመጣ የሚከላከልባቸውን መጋብርት ከመስጠቱ ላይ ዳ ይላሉ። ይህም ዳ ማለት ያለ አንድ ነገር አይደለም። ሕዝብ ላይ ካላቸው ከአሰተኃቅሮ የሚመነጭ አመለከካከት የተነሳ፤ ሕዝብ በተጨባጭ በመብቱ ሲያዝ፤ሲናዝዝ፤ሲሸር ሲሾም፤ ሲነቅፍ ሲተች አይታያቸውም። መብት ካገኘ ሕዝብ አይቻልም፤ በመብቱ ባግባብ መጠቀም አይሆንለትም፤የጮሌዎች መጠቀሚያ፤የከበርቴዎች መሳሪያ ይሆናል፤የእኛ ሕዝብ አልተማረም፤ደንቆሮ ነው፤...ምክንያቱም ይዥጎደጎዳል፤መላቂያም የለውም። ነገር ነገሩማ ውቃቢ መልዓክህ ሆነን ከክፉ ልንጠብቅህ ወደ በጎ ልንመራህ እንችል ዘንድ ሥልጣን ከሰማየ ሰማያት ወርዶ በእኛ ላይ ያደረ የባህርይ ገንዘባችን ነውና ሥልጣንን አትመራመር፤ የሥልጣናችን መግለጫ የክብራችን መከሰቻ ሁነህ የተሰጠኸን ነህ ማለታቸው

መሆኑ ነው፡፡ ሕዝብ ያለ ሞግዚት ራሱን ችሎ ሲተዳደር ከቶ አይታያቸውም፡፡ ይህን ከባድ ኃላፊነት ራሳቸው ላይ በራሳቸው ከቆለሉ በኋላ በሥልጣን ደጃፍ ዝር ሚል፤ አሻቅቦ የሚናገር ምሱን ማግኘቱ የግድ የሚከተል ነው፡፡”

ይህ ያኔ የተላላፈ መልዕክት ዛሬም ሀቅ ነው፡፡ ከወያኔም ሆነ ተቃዋሚ ነን ከሚሉ አንዳንዶች አንፃር ልናጤነውም የሚገባ ነው፡፡ ይኸው የዴሞክራሲያ ዕትም ትችቱን በመቀጠል ያስተላላፈውም መልዕክት የኢሕአፓን የዛሬንም አቋም ከዴሞክራሲ ትግል አንፃር  ገልፅ የሚያደርግ ነው፤

“ በዴሞክራሲያዊ ሥርዓት የበላይ ገዢ ሕዝብ እንደ መሆኑ መጠን፥ ለዚያ የበላይ አካል፤ ልዩ ልዩ አስተሳሰብና ልዩ ልዩ ንድፈ ኃሳብ፤ ልዩ ልዩ ዕቅድ፤ ልዩ ፕሮግራም...ወዘተ እየቀረበለት፤የያንዳንዱን ያስተሳሰብ ዘርፍ ሕፀፅ ምልዓቱን ዓይቶ የሚበጀውን ሊያቅፍ፤ሊመርጥ ሊያማርጥ ካልቻለ፤ ልዩ ልዩ አስተሳሰብ የሚያንፀባርቅ ሕዝብ ምርጫው አንድ ፓርቲ ብቻ በሚሆንበት አግባብ ዕርቅ፤ስምምነት፤ሰላም ሊኖር ከቶ አይችልም፤አልቻለምም፡፡ ከዚህም ዘንድ የአንድ ፓርቲ ወይም ቡድን የብቻ ገዢነት አክትሞ የሕዝብ ድጋፍና አመኔታ ያገኙ ፓርቲዎች የሚሳተፉበትን ከቀሩት የላቀ የሕዝብ ድምፅ አግኝቶ ሀገሪቱን እንዲመራ ሚዛን የደፋው ፓርቲ ደግሞ ሥልጣኑን ከሕዝብ ፍላጎት ና ከተቀበለው አደራ  ውጭ ያለ አግባብ እንዳያውለው ሌሎቹ ፓርቲዎች ማዕገት ሁነውበት፤ ሀገሪቷ ዕድሏ ዳግመኛ ከጥቂት አምባገነኖች እጅ ወድቆ እስካሁን የተጎነጨችውን መራራ ፅዋ እንዳትጋት የሚያደርጋትን ሥርዓተ መንግስት መከተል ብቻ ነው  ኢትዮጵያን የሚበጃት ብሎ ኢሕአፓ ለዚህ ተልዕኮ በቁርጠኛነት ይታገላል፤ለዚሁ ዓላማ ከቆሙትም ጋር ይተባበራል፡፡”

የኢሕአፓ መልዕክት ዛሬም ይህ ነው፡፡ ዴሞክራሲ ለሰፊው ሕዝብ አለገደብ!